# ይቅርታ

## ከስታሊን እስከ መለስ

የቅንጅት መሪዎች ከመከረኛው ቃሊቲ ሲፈቱ የተፈቱበትን ሥርዓት በተመለከተ መለስና ሰዎቹ ያሉትን ብዙም ሰው ጉዳዩ ያለው አልነበረም። ከ17 ዓመታት በሁዋላ ሰዎቹ (እነ መለስ) ምን እንደሚያስቡና ምን እንደሚያደርጉ መረዳት ለብዙዎቻችን ያን ያህል ከባድ አልነበረም። በነዚህ ዓመታት ብዙ ሕወሃት ወለድ መራራ ቀልዶችና ተውኔቶች ያስተዋልንባቸው ነበሩ። በቅርቡም የወይዘሪት ብርቱካንን ዳግም መታሰር ሲያውጁም የገዢዎቻችንን "የፖለቲካ ጠቢብነት" ከቀድሞው መጽሃፋቸው አንድ ገጽ ገለጥ አድርጎ ከማንበብ ያለፈ እንዴት ብሎ የሚገረምም ብዙ የለም። ትንሽ ቢያስገርመን አልያም ለራሳችን ጥያቄ የሚጭርብን ነገር ቢኖር የእኛዎቹ የስታሊን ደቀ መዛሙርት ሩሲያውያን እንኳን የሰውዬውን ነገር ከተዉት ዓመታት በኋላ ያረጀን ውሻ አዲስ ብልጠት አያስተምሩም እንዲሉ ዛሬም የትናንት ከትናንት ወዲያውን የፖለቲካ ቧልት በአዲስ መልክ ማቅረባቸው ነው።

የቅርቡ የወይዘሪት ብርቱካን ዳግም እስር ጉዳይን ለብቻው፣ የቅንጅት መሪዎችን "የይቅርታ" ጥያቄና በጥቅሉ ትናንት የተጀመረ የፖለቲካ ተውኔት አይደለም። ብዙም ሳንርቅ በ1988 ዓ.ም. ገደማ የቀድሞው ጠቅላይ ሚንስትር ታምራት ላይኔ ከወራት የቤተ መንግስት የቁም እስር በኋላ በአንድ "የተረገመ" ቀን "ፓርላማ" ቀርበው እንዴት ከፓርቲ መስመር ወጥተው "ስኳር" ጉድ እንዳደረጋቸው መናዘዛቸውን ብዙዎቻችን የምናስታውሰው ነው። የገዢው ቡድን "ሁለተኛ" ሰው እንዲያ ራሳቸውን ያዋርዳሉ ብሎ ያለመም የገመተም አልነበረምና በጉዳዩ ያልተደመመ ቢኖር ጥቂት ነበር።

ለነገሩ ቅድመ ታምራት ላይኔ ግምገማ እየተባለ ሕወሃት በትረ መንግስቱን ከያዘ ጀምሮ ልቡ ከራሱ ጋር ያልሆነውን ሁሉ እያስለፈለፈ ራሱን እያስከሰሰ የሚታሰረው ሲታሰር በረሃብ የሚቀጣውም ከስራ ተፈንግሎ ከነቤተሰቡ ሂሳቡን እንዲያወራርድ ሲደረግ ነበር የኖረው። የሕወሃት ሰዎች ቅድመ አራት ኪሎ በጫካ ሳሉም ይህንን ስታሊናዊ ግምገማ በፖለቲካዊም ሆነ ወታደራዊ አመለካከቶች ያፈነገጠ ሃሳብ የነበራቸውን አመራሮቻቸውንና ተራ አባላት ከጨዋታ አስወጥተውበታል። ከዚያም ባለፈ ሰራዊታቸው እርስ በራሱ እንዲሳለል በማድረግ ፍጹም የሆነ የመንፈስ ባርነትን ለራሳቸው ደግሞ ፍጹም የሆነ ሥልጣንን ለብሰውበታል።

ወደ ነገራችን ስንመለስ ልክ እንደ አቶ ታምራት እ.ኤ.አ. በ1936 ገደማ ከስታሊን ታላላቅ ባለ ስልጣናት መሃከል አንዱ እንዲሁ ፓርቲውን በመከፋፈልና በታላቁ መሪ ስታሊን ላይ በማሴር ተከሰው በሚስጥራዊው ፖሊስ አበሳቸውን ካዩ በኋላ "ኮንግረስ" ፊት ቀርበው ይናዘዛሉ። ያም አላበቃም ጉዳዩ ወደ "ፍርድ ቤት" ይመራል። ፍርድ ቤትም ቀርበው ራሳቸውን ምድር ልትፈጥረው በምትችለው ሁሉ ይከስሳሉ። "እኒህ የፖለቲካ ሰው ፖሊስ ካስጠናቸው ራስን የመክሰሻ ማስረጃዎች አንዱ የስታሊን ቀንደኛ ደመኛ የነበሩትን ትሮትስኪ በ1932 ዴንማርክ ኮፐንሃገን ከተማ ብሪስቶል በተባለ ሆቴል አግኝተዋቸው እንዳሴሩ ይናዘዛሉ። ችግሩ ታዲያ ወዲህ ነው የተጠቀሰው ሆቴል በተባለው ዓመት በከተማዋ አልነበረም፤ በ1913 ፈርሶ ኖሯል። ስታሊን ይህንን ሲሰሙ

በንዴት ጦፈው የጸጥታ ሹማቻቸውን ደደብ ካልጠፉ ባቡር ጣቢያ ሆቴል ታስጠናዋለህ?" አሉት ይባላል።

ሕወሃት የኢትዮ/ኤርትራ ጦርነትን ተከትሎ ለሁለት ሲሰነጠቅ ከዚሁ ራስን ከመክሰስ ባለፈ ሌላ የስታሊን ጨዋታ ይዘው ብቅ አሉ። ይቅርታ! በወቅቱ አፈንጋጮች ከሚባሉት የእነ ስዬ ወገን ለነበሩት የሕወሃት ሰዎች በስተመጨረሻ የቀረበላቸው አማራጭ ወይ ይቅርታ፣ አልያም አንገትን ሰብሮ መቀመጥ ካልሆነም ሃገር ጥሎ መሄድ ወይም እስር ነበር ይባላል። ልጆቼን እንዴት አሳድጋለሁ ያሉት እነ አባይ ፀሃዬና ሃሰን ሺፋ ሶስት መቶ ስድሳ ዲግሪ በቀናት ውስጥ ዞረው ለአቶ መለስ የይቅርታ ደብዳቤ ይጽፋሉ። የአቶ መለስና በረከት ቡድን በተቆጣጠረው የመገናኛ ብዙሃን ይህንኑ የይቅርታ ጥያቄ በኩራት እየለፈፈ እስከ ተራ የህወሃት አባላት ድረስ ከነ ስዬ ወገን የነበሩትን መንፈስ ለመስበር ተጠቅሞበታል፤ ፋታ አግኝቶ ቀጣዩን የምንጠራ ሥራ እስኪ ጀምር ድረስ። የዛሬው የአዲስ አበባ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳም የዚሁ የይቅርታ ጨዋታ ተጠቃሚ ናቸው። በወቅቱ ከነ ስዬ ወገን በሃሳብ በመቆማቸው በአንድ ሌሊት ከሚንስትርነት ቁልቁል ወርደው በኢሚግሬሽን ተራ ኤክስፐርት ሆነው ለወራት የአቶ መለስን አምላክ ምህረት ተማጽነዋል።

እነ አቶ መለስ በተማሪዎች እንቅስቃሴ ወቅትና በረሃም ከገቡ በኋላ የስታሊንን የሶሻሊዝም ፍልስፍና ብቻ ሳይሆን የሰውዬውን የአገዛዝ ስልቶች አንድ በአንድ ሳያጠኑም አልቀረም። የፖለቲካ ርዕዮታቸው እንደ ዛሬው ጠዋት አብዮታዊ ዲሞክራሲ ማምሻውን ደግሞ ነጭ ካፒታሊዝም እየተባለ ማደናገር ሳይጀመር በፊት የስታሊንና የአልባኒያ ሶሻሊዝም ድቅያ መሆኑ በኩራት ይለፈፍ ነበር። የይቅርታውም ፌዝ የተቀዳው ከወደዚያው ለመሆኑ የሚከተለው ታሪክ ያስረዳናል። እ.ኤ.አ. በ1938 ገደማ ከሶቭዬት ኮምኒስት ፓርቲ ፖሊት ቢሮ አባላት መካከል አንዱ የሆኑትና በተሰሚነትም ከስታሊን የላቀ ተቀባይነት በኮምኒስት ፓርቲው አባላትና በህዝቡም የነበራቸውን ቡካሪን የተባሉ ፖለቲከኛን ስታሊን ከመንገዳቸው ለማራቅ ይወጥናሉ። በወቅቱ ሶቭዬት ሩሲያ በከባድ የኢኮኖሚ አጣብቂኝ ውስጥ ወድቃ የነበረችበትና ስታሊን በስሜት የጀመሩት የመንደር ምስረታ የእርሻ ምርት እጥረትን አስከትሎ ከባድ የምግብ እጥረት ያጋጠመበት ወቅት ነበር። በተቃራኒው ቡካሪን ገበሬዎች በገዛ መሬታቸው የሚቆዩበትንና የስታሊን የመንደር ምስረታ ፖሊሲን አጥፊነት ይተቹ ነበር። በእርግጥም ሶቭዬት ሩሲያ ከከፋ ረሃብ ወደ በኋላ ያመለጠችው በዚሁ ስልት ነበር።

ስታሊን በዚህም በዚያ ብለው እኚህን የፖለቲካ ተቀናቃኛቸውን ለእስር ያውሉና በሚስጥራዊው ፖሊስ አሸት አሸት አስደርገው ኮምኒስት ፓርቲው ኮንግረስ ፊት ያቀርቧቸዋል። ሰውዬው ለረሃቡም ለቅርብ ጓደኛቸው ሌኒን ሕልፈተ ህይወትም ራሳቸውን ከሰው ፓርቲውን ይቅርታ ይጠይቃሉ። ለስታሊን ይህ የሚቀጥለውን ጨዋታ ለመጀመር በቂ ነበር። በወራት ዕድሜ ውስጥ ሰውዬውንም እስከ መንደር ካድሬ ድረስ የርሳቸው ደጋፊ የነበረውን በሙሉ የታደለ ሳይቤሪያ ለግዞት ያልታደለ ደግሞ በየመንገዱ ለሚስጥራዊው ፖሊስ እራት ሆነዋል።

አቶ መለስም የእነ ስዬን ወገን በሃሳብም በመንደር ልጅነትም የደገፉትን አንድ በአንድ ለቅመው ከፓርቲ ጨዋታ አውጥተው መቀጣት ለሚገባቸው ሁሉ ቀጥተዋል።

እንግዲህ የቅንጅትን ሰዎች "ይቅርታ"ን የተመለከትን እንደሆነ የዚሁ የስታሊን ወለድ ጨዋታ ቅጥያ ለመሆኑ ብዙም መመራመር አያስፈልገንም። እነ መለስ የሚሆንላቸው ከሆነ ተቃዋሚዎቻቸውን በውድም በግድም በማጭበርበርም ይቅርታ ያሰኙ እንደሆነ ከመሪዎቹ ይቅርታ የበለጠ ከዚያ የሚለጥቀው ሕዝብን ወይንም ደጋፊን የማሸበር፣ የመመንጠርና ፀጥ ለጥ የማሰኘት ዕቅዳቸው ነው። አሁን እንደምናየው በየፖለቲካ ምዕራፉ ለአገዛዝ አልመች ያሉ ግለሰቦች፣ የፖለቲካ ተቋማትና ሃገራዊ ተቋማት በሙሉ የምንጠራ ዘመቻ ይካሄድባቸውል። ምርጫ 97ን ተከትሎ የትኛውም የዲሞክራሲ እንቅስቃሴው አካል የሆነ ወገን ሁሉ ከምንጠራና መቀጣጫ አላመለጠም። ይህ በህጋዊ በሚሉት መንገድም ዓይን በአወጣ አፈናም እስከ ቀበሌ ድረስ ተከናውኗል እየተከናወነም ያለ ነው። በየመንግስት መስሪያቤቱና ፋብሪካዎች ቢዝነስ ኢንጅነሪንግ በሚሉት ግምገማ ከሕወሃት ወገን ልቡ ያልሆነው ሁሉ እንጀራውን እንዲያጣ እየተደረገ ነው። ሕጋዊ በሚሉት ሽፋን ደግሞ ሲቪል ማህበራትንና የተራድኦ ድርጅቶችን የማክሰም ተግባርን በቅርቡ የታዘብነው ነው። እንግዲህ የወ/ሪት ብርቱካንንም እስር ደግሞ ከዚሁ አንጻር መመልከቱ ተገቢ ነው የሚሆነው። የወ/ሪት ብርቱካን ዋንኛ ጥፋት በህወሃት ዓይን ይቅርታ ጠይቀው ሲያበቁ እንደ አቶ ኩማ ደመቅሳ አልያም ታምራት ላይኔ ወይ መለስን አለማገልገላቸው አልያም ፖለቲካ ለምኔ ብለው "ጌታን" አለመቀበላቸው ነው። በነአቶ መለስ ዓይን ይቅርታ የጠየቀ ሰው መጸጸቱን በነዚህ መንገዶች ነው የሚያሳየው። የፖለቲካ ፓርቲ መስርቶ ደግሞ እነሱን መገዳደር ከጀመረማ ምኑን ይቅርታ ጠየቀው? ለዚህ ነው የአዲስ አበባ ሰው ሲቀልድ ወ/ሪት ብርቱካን ስዊድን ሄደው ስለ ይቅርታው ማብራሪያ ባይሰጡም ሰው በመኪና ገጭተውም ቢሆን ቃሊቲ መውረዳቸው አይቀርም ነበር የሚለው። የቅርቡን የቴዲ አፍሮን ሳታመሃኝ ብላኝ እያስታወሰ።

በፖለቲካ ተሳትፎአቸው ምክንያት የወ/ሪት ብርቱካንና ሌሎችም የፖለቲካ ሰዎች እስር በሕዝብ መገናኛ ብዙሃን ዓይን አትኩሮት ውስጥ ገባ እንጂ እነ አቶ መለስ በየዕለቱ ኮሚክ የሆኑ ተውኔቶችን ለተመልካቹ ማቅረባቸውን እንደቀጠሉበት ነው። የኦፌዴኑ አቶ በቀለ ጅራታና ሌሎች ሰዎች አብረዋቸው ሲታሰሩ ተገኘ ያልተባለ ማስረጃ ዓይነት አልነበረም። የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ፣ ባለ300 ገጽ የፖለቲካ ሰነድ፣ የጦር መሳሪያዎች ሁሉ። ታዲያ በነመለስ ተውኔት ውስጥ ሁልጊዜም ራሱን የሚከስ ወገን አይጠፋም። በአሸባሪነት ተከሰሱ የተባሉ ምስኪን ሰዎች ምናልባትም ከዚያ ቀን በፊት በዓይናቸው አይተውት የማያውቁት መትረየስና የመገናኛ መሳሪያ ይደረደርና በድብደባ ያጠኑትን ለቴሌቪዥን ካሜራ ይናዘዛሉ። ፍርድ ቤት ሳይሄዱ በቴሌቪዥን ችሎት ጥፋተኛነታቸው ይረጋገጣል። ለነገሩ ፍርድ ቤትስ ሲኖር አይደል? ታዲያ እንዲህ ዓይነቱ የኬጂቢ ጨዋታ አሁንም መልሶ ወደ ዘመነ ስታሊን ይወስደናል። ስታሊን የሲጋራ ፒፓቸው ይጠፋና ለፖሊስ አዛዣቸው በአስቸኳይ አፈላልጎ እንዲያመጣላቸው ሴረኞቹንም እንዲያቀርብላቸው ያዙታል። እንደ ወያኔ ካድሬዎች ከነፋስ የሚፈጥኑት የስታሊን ፖሊሶች እዛው ቤተመንግስት ውስጥ እንኳን ፒፓውን ለመፈለግ ውልም አላላቸው። ወደ በኋላ ሰውዬው የፖሊስ አዛዣቸውን አስቀርበው የፒፓውን ጉዳይ ከምን እንዳደረሰው ይጠይቁታል፤ አስር ተጠርጣሪዎች ተይዘው እየተመረመሩ እንደሆነ ይነግራቸዋል። ወደ ማርፈጃው ስታሊን ለአዛገፉ ደውለው ፒፓውን ቦት ጫማ ውስጥ እንዳገኙት ይነግሩትና ተጠርጣሪዎቹን እንዲፈታ ይነግሩታል። የፖሊስ አዛገፉ ደንገጥ ብሎ ጌታዬ ሰባቱ እኮ አምነውል አላቸው ይባላል። ህወሃት የቅንጅት ሰዎች 193 ሰዎችን በጠራራ ፀሃይ ራሱ ለገደለበት ወንጀል አምነዋል አይደል ያለን?

ቸር እንሰንብት

samsonbrh@gmail.com